ባስቸኳይ ይፋ እንዲወጣ

ሶማሊያ፦ የጦርነት ወቅት ወንጀል በሞቃዲሾ

የተባበሩት መንግስታት በህዝብ ደህንነት ጥበቃ ላይ ማትኮር አለበት።

(ናይሮቢ፦ ኦገስት 13፣ 3007) የኢትዮጵያና የሶማሊያ ወታደሮች፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ የአመፀኛ ሃይሎች በአሁኑ ጊዜ ሞቃዲሾ ውስጥ የጦርነት ወቅት ሕግጋትን በመጣስ በህዝብ ላይ ከፍተኛ በደልና ስቃይ ማስከተላቸውን የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ (ሂዩማን ራይትስ ዋች) በዛሬው ዕለት ይፋ ባወጣው ሪፖርት አስታውቋል። በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት የሴኪዩሪቲ ካውንስል የሶማሊያን ሁኔታ ገምግሞ የሰላም ጥበቃ ኃይል ለመላክ ሲወስን የህዝብ ደህንነት ዋስትናንም ትኩረት እንዲሰጠው የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ አጥብቆ አሳስቧል።

በ113 ገጾች የተጠናቀረው "የሞቃዲሾ ህዝብ ጥቃት" የተሰኘው ሪፖርት ለመጀመሪያ ጊዜ በስፍራው የተካሄደ ምርመራ ሲሆን፤ ባለፉት ማርች እና ኤፕሪል 2007 በሞቃዲሾ  ተካሂዶ የነበረ ውጊያ ስላደረሰው ከፍተኛ ጥፋትና በመቶ ለሚቆጠሩ ሰዎች እልቂትና ለአራት መቶ ሺህ ሰዎች ስደት ምክንያት መሆኑን ይዘግባል።

የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ዋና ዳይሬክተር ኬን ሮዝ እንዳሉት "በውጊያው የተሳተፉት የተለያዩ ኃይሎች በከተማው ለሚኖረው ህዝብ የነበራቸው ግዴለሽነት ወንጀለኛ ያደርጋቸዋል። ይብሱን ደግሞ የተባበሩት መንግስታት ሴኪዩሪቲ ካውንስል ለዚህ ወንጀል ያሳየው ደንታቢስነት በደሉን የከፋ ያደርገዋል።"

የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ባካሄደው ምርመራ፤ በጊዜው የተፈጸሙ በርካታ የጦርነት ወቅት ወንጀሎችን ዘግቧል። ለምሳሌ በሶማሊያ ሽፍቶች ከተፈጸሙት ሕገወጥ ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፦ በርካታ ነዋሪዎች ካሉበት መንደር ሞርታር መተኮስና ታጣቂዎችን ማሰማራት፣ የሶማሊያ የሽግግር መንግስት አባላትን አድኖ መግደል፣ የጦር ምርኮኞችን ሰብስቦ መፍጀትና አካላቸውን መቆራረጥ።

የሶማሊያን የሽግግር መንግስት የሚደግፈው የኢትዮጵያ ጦር አባላትም እንዳሻቸው ሞቃዲሾ ውስጥ የህዝብ መኖሪያ አካባቢዎችን በሮኬት፣ በሞርታርና መድፍ በመደብደብ፤ ወታዶሮቹም ሆስፒታሎችን በመውረርና የህክምና ቁሳቁስን በመዝረፍ፤ አንዳንዴም ይሁን ብለው ግለሰቦችን በመግደል የጦርነት ወቅት ሕግጋትን መጣሳቸውን የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ አረጋግጧል።

የሶማሊያ የሽግግር መንግስት ኃይሎች ከኢትዮጵያ ጦር ዝቅተኛ ቦታ ቢኖራቸውም፤ ውጊያ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ኗሪዎች በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠት፣ የህዝብን ንብረት በመዝረፍ፣ ለተሰደዱ የከተማው ሰዎች ለሚደረጉ እርዳታዎች እንቅፋት በመፍጠርና በእስራት ላይ የሚገኙ ዜጎችን በማጎሳቆል ወንጀል ፈጽመዋል።

“ሽፍቶች ከህዝብ መሃል ተሰማርተው እንደነበር ግልፅ ቢሆንም፣ በዚህ ሳቢያ የኢትዮጵያ ጦር የነዋሪዎችን መንደር በሮኬትና በቦምብ መደብደብ አይገባውም ነበር።” ሲሉ የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ዳይሬክተር ተናግረዋል።

ይህ የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ዘገባ ይፋ የወጣበት የዛሬው ቀን፣ የተባበሩት መንግስታት የሴኪዩሪቲ ካውንስል የሶማሊያን ጉዳይ ለመመልከት ጉባዔ የሚከፍትበት ዕለት ነው። የሴኪዩሪቲ ካውንስሉ በጉባዔው ወደ ሶማሊያ ስለሚላከው ባለ1500 አባላት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተልእኮ እንደሚነጋገርና፣ ይህንንም ተልእኮ የተባበሩት መንግስታት ኃይል ለማድረግ እንደሚወያይ ይታወቃል።

የሶማሊያ የሽግግር ፌዴራላዊ መንግስት በኢትዮጵያ ተደግፎ በሞቃዲሾ በጃንዋሪ 2007 ስልጣን ከጨበጠ ወዲህ ከከተማው ውስጥ ውጊያ እየተባባሰ መጥቷል። በዲሴምበር 2006 የኢትዮጵያ ጦር በዩናይትድ ስቴትስ ድጋፍ የእስላማዊ ፍርድቤቶችን ቅንጅት አመራር ከሞቃዲሾና ከማዕከላዊ ደቡብ ሶማሊያ ፈንቅሎ አስወጥቷል።

ከጃንዋሪ 2007 ጀምሮ የእስላማዊ ፍርድቤቶች ታጣቂ ሚሊሻዎችና የተባበሩ የአመፅ ወገኖች በአጥፍቶ የመጥፋት ጥቃትና የሽግግሩን መንግስት ሲቪል አባሎች በመግደል ሽብር በማካሄድ ላይ ናቸው። በተጨማሪም ሽፍቶቹ ከሞቃዲሾ ህዝብ መሃል ተደብቀው ሞርታር በመተኮስና የህዝቡን ደህንነት ከአደጋ ላይ በመጣል የጦርነት ወቅት ሕግጋትን አፍርሰዋል።

በማርች 29 ቀን የኢትዮጵያ ኃይሎች ሁለት አቢይ የፀረ-ሽፍታ ዘመቻዎችን በሞቃዲሾ አካሂደው ነበር። በእነዚህ ዘመቻዎች ለሰላማዊ ህዝብ ግዴለሽነት በተሞላበት ሁኔታ ሽፍቶች የሚገኙባቸውን መንደሮች በሞርታር፣ በካቱሻ ሮኬቶችና በመድፍ ደብድበዋል።

ከኤፕሪል18 እስከ 26 በተካሄደው ሁለተኛ ዘመቻ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሌሎች የከተማውን አካባቢዎች ዒላማ በማድረግ ከፍተኛ ጥፋትና በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎችን እልቂት አስከትለዋል። በሁለቱ ውጊያዎች ምን ያህል የከተማው ኗሪዎች ህይወታቸውን እንዳጡ በትክክል ባይታወቅም 1300 ያህል ሰዎች መገደላቸው ይገመታል።

የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ ጉዳይ ለመግባቱ ምክንያት የአካባቢው ፀጥታ መደፍረስ ለኤርትራ የእጅ አዙር ጥቃት የሚፈጥረው የተመቸ ሁኔታ፣ እንዲሁም ሁለት የኢትዮጵያ የአመፅ እንቅስቃሴዎች ሶማሊያ ውስጥ መግባታቸው ነው።

በጃንዋሪ 2007 የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በደቡብ ሶማሊያና ኋላም በሰሜን ምስራቅ ፑንትላነድ ተደጋጋሚ የአየር ጥቃት አካሂዷል። እነዚህ ጥቃቶች የአሜሪካ ጦር ከሶማሊያ በ1994 ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የመጀመሪያዎቹ ናቸው። የሶማሊያ የእስላማዊ ፍርድቤቶች ለአንዳንድ ከአለም አቀፍ የሽብር አውታር ጋር ግንኙነት ላላቸው ግለሰቦች፣ ለምሳሌ በ1988 ኬንያና ታንዛኒያ ውስጥ የዩናይትድ ስቴትስ

ኤምባሲን በቦምብ ላጠቁት ሰዎች መጠለያ ሆኗል ሲል የአሜሪካ መንግስት ወንጅሏል።

“ዋነኛው የመጀመሪያው ውጊያ በኤፕሪል ካለቀ በኋላ የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግስት ወታደሮች በየቦታው የህዝቡን መብት እየረገጡ ይገኛሉ” ብለዋል የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ዳይሬክተር ኬን ሮዝ። “ዘላቂ የፀረ-ሽብር መፍትሄ የሚገኘው ሰብአዊ መብቶች ሲከበሩና ወንጀል ለፍርድ ሲቀርብ ብቻ ነው።” የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግስታት የሚያካሂዱትን የማን አለብኝ ሕገ-ወጥነት ይገቱ ዘንድ የተባበሩት መንግስታትን ሴኪዩሪቲ ካውንስልና ሌሎች አበይት የአለም አቀፍ ድርጅቶችን እንዲያስገድዷቸው የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ አሳስቧል።

ሁኔታው ያሳሰባቸው አገሮችም የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ተቆጣጣሪና ዘጋቢ ተልእኮ እንዲፈጥርና ወደ ሶማሊያ እንዲልክ መጠየቅ፤ እንዲሁም አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

“የሞቃዲሾ ህዝብ ጥቃት” በሚል ርዕስ የቀረበውን የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ዘገባ ለመመልከት የሚከተለውን ይጎብኙ፦

http://hrw.org/reports/2007/somalia0807/

የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ በዘገባው ላይ ያቀረበውን አስተያየት ለማዳመጥ የሚከተለውን ይጎብኙ፦

http://hrw.org/audio/2007/english/somalia08/somali16599.htm